EthioLion

# የአንበሶች ቅርጫ

የጐንቻው !

መላ አውሮፓዊ የነጭ ዘር ዶልቶ፣አገር በቅርጫ በልቶ፣
እንግሊዝ፣ጣሊያን፣ስፓኝ፣ፈረንሳይ፤ፓርቹጋል ዳጉቶ፣
መላ አፍሪቃን ሊገዛ፣ተቀራምቶ፣ ከነዜጐቿ ቀምቶ፣
ውሉን ሸርበ ሴራ፤በኃይሉ ተመክቶ፣በትዕቢቱ ተንጠራርቶ።

ከፈጣሪ ከአምላክ ፈቃድ አፈንግጦ፣
የብስ ባህር ውቅያኖስ ጠፈር አቋርጦ፣
በገፍ ጦር ጭኖ መርዝ በጥብጦ፣
ከርሱን ሊያቃፍት በግፍ ቀላውጦ፣
ቅኝ ሊገዛ ደም ሊያፈስ ቋምጦ፣
ሊሸጥ ሊለውጥ ‘ባሪያ’ አርጐ ረግጦ፣
ጦር አዘነበ በአፍሪቃዊያን፣በጥቁር ዘር አሳግጦ።

የኛም አገር የአበሻ ምድር ለ‘ቅርጫ’ ወድቆ፣
‘ቁርጥ’ ሊሆን ‘ዳረጐት’ በ‘አንበሶች’ተቦጫጭቆ፣
የዘመናት ታሪኳ፣አንደነቷ፣ ባህል-ኀዝቧ ተንቆ፣
በቆየ ቂም በመንጋ ‘ነጫጭባ’ ‘ደባው’ ጸድቆ፤
የውጫሌው ፍርደ ገምድል አንቀጽ ሰርቆ።

በአፈሯ ሻቅሎ በአየሯ ሰክሮ፣
ንጉስ ህዝባቸው አልሞ መክሮ፣
ትጥቅ ቀለቡን በመርከብ ቋጥሮ፣
ገባ ‘መሰዋ’ ቀይ ባህራችንን ተዳፍሮ።

ጀነራሎች፤ የጦር አበጋዞች ጨካኞቹ ተመርጠው፣
እነ ‘አልበርቲኒ’፣‘ባርቴሪ’ በሃያ ሺዎች ታጅበው፣
የግብጹ እስማኢል በተቀጣበት አርጐው በ‘ጉራ’፣
ሞት ሸተው መጡ ከአፄ ዮሐንስ ከጀግናው ሥፍራ፣
‘ሶላቶው’ጣሊያን ገፍቶ መሸገ በ‘አዴግራት’ ጐራ።

ቃል ሰጥቷልና ለሮማው ገዥ በደርሶ መልሱ፣
‘አበሻን’ ፈጅቶ ንጉሱን ሊያቀርብ ከነነፍሱ፣
አፄ ምንይልክን በ‘ሽቦ ቅርጫት’ አስረው ሊያደርሱ፣
ለመዝናኛ መጫዎቻቸው በሮማ ሀገር ለንጉሱ፣
እንዲህ ነበር ንቀው ተሳልቀው ‘አድዋችን’ የደረሱ፤
በራሳችን በአገራችን ጦር ሰብቀው የኰነሱ።

ይኸንን ቢሰሙ የሸዋው ንጉስ አባደፋር፣
አፄ ምንይልክ የአንበሳው አምሳል የአበሻው ዘር፣
ክተት አወጁ፣አስጐሰሙ ነጋሪት አስመቱ፣ከበሮ፣
እቴጌም ጣይቱ ግብር አሰናዱ በድንኳን በዳሮ፣
ተከተለኝ አሉ ሁሉም ተዳረሰ፣የፃድቃን ቀጠሮ።

ከአራቱ ማእዘን ጀግናው ተፎካክሮ፣
በቅሎውን አላብሶ፤ጋሻውን ጠድሮ፣
ጥምጣሙን አዙሮ፤ሳንጃውን ቀስሮ።
ለሸኑን፣ወልውሎ ሰቦ ውጅግራውን
ወገቡን ጠምጥሞ ዝናር ጀበርናውን

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

የጥንት የአባቶቹን ዱካ ተከትሎ፣
ሽቅብ አጋመረ ሰደድ ተቀጣጥሎ፤
እየተወባራ ፎክሮ እያገሳ፤
በየመሪው ሆኖ አንበሳው ተነሳ።

የራስ መኰንኑ የሐረሩ ጦር፣
አልፎ ‘ወራይሉ’ ደርሶ በግምባር፣
በ ‘ዶጋሌ’ መልክዓ የራስ መንገሻው፣
የ ‘ዮሐንስ’ በኩር የትግራይ መሪው፣
ደፍጦ ‘አምባለጌ’ ላይ ጠላቱን ፈጀው፣
የ ‘ተክለ ሃይማኖት’ የ ‘ጐጃሙ’ አርበኛ፣
የ ‘ራስ ሚካዒሉ’ የወሎው’ ቁርጠኛ፣
የኢትዮጵያ መድኅኖች የጠላት መጋኛ።

በሦስቱ ማእዘን ሲቆሰቁስት፣ሲያርገበግቡት፣
ቆልተው ሲያሳርሩት አቃልጥለው በአፎት፣
አፄም ምኒልኩ፣እቴጌ ጣይቱ ደርሰው በጠዋት፣
ተሳልመው ተማጽነው ‘አባ ገሪማውን’ ገድሉን ታቦት፣
ነጭ ሻማ ለብሰው ሊቀ መኳስ መርተው፣
አሹነ ማቲወስን ደጀን አስከትለው፣
ባርከው ቀደሱለት መሃል ጦሩን ገብተው፣
ከጠላት ከንድተው ውጊያ ስልት ነድፈው፣
ከፊትና ኋላ ከበው አቋራርጠው፣
አደነባበሩት ሁለት ብርጌድ ከፍለው።

የአልበርቶኒውን ጦር ሸጥ በሸጥ ነድተው፣
የባርቴሪንም ጦር ጉሮሮው ዘግተው፣
የአበሻው ባለሚል በልጠው ጠብበው፤
የውጊያው ሊቃውንት አገር ያፈራው፣
እንዲያ ጉድ አረጉት አጉል ተንቀው።

ቀበሌው በሩምታ በቀውጢው ሲሻማ፣
ጋራው ሲናቃነቅ በመድፍ ሲያግማማ፣
ሰማይ በጢስ ዳምኖ ቀን ሲሆን ጨለማ፤

ምድር ቃውጢ ሲሆን አቧራው ሲነሳ፣
ተቆላልፎ ሲወድቅ ሬሳ በሬሳ፣
አየሩ ባሩዱ ወበቅ ሲከረፋ፣
አሞቱ ሲንጫረር ሳቶኑን ሲተፋ።

‘የጦሩ ገበሬ’ ገባ እየፎከረ፣
በጐራዴው አንገት እየሰባበረ፣
በሳንጃው ሆድእቃ እየበረበረ፤
ደም ጠምቆ ጠላቱን ግቶ እያሰከረ
ኃያሉ አበሻ ገድሉን አበሰረ፣
የአያት ቅድመአያቱን ድሉን አዘከረ።

በ ‘ኢሻሾ’፣‘ባላህ’ በአድዋ ቋጥኞች፤ሸለቆ ተራራ፣
ዶጋሌ፤አምባለጌ፤በቦሩሜዳ ላይ አፅሙ የተዘራ፣
በየ ‘መልከዓ’ው ውለው የተሰውት ጀግኖች ታላቅ ገድል ሥራ፤
ሆኖ ይከበራል ትውልድ የሚያኰራ።

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

*ሺህ ጠላቱን ገድሎ አሳዶና ማርኮ፣*
*ኃያሉን ወራሪ የረታ አፍረክርኮ፤*
*አስገበረ ካሳ በውል አንበርክኮ።*

*ደም አፈሩን ሆኖ ነፍሱ የጸደቀ፣*
*ጀግናው ማንነቱን በዓለም ያሳወቀ፣*
*ድንበሩን፤ወገኑን ክብሩን ያስጠበቀ፣*
*ሀገሩን ከ'አንበሶች መንጋጋ' ወግቶ፤የነጠቀ፣*
*ለመላው አፍሪቃ ጉህ አስፈነጠቀ።*

*ጀግናው ታሪክ ክብሩን አንድነት ሰንድቆ፣*
*ትውልድ ከትውልድ ወዳጅ ጠላት አውቆ፤*
*ኢትዩጵያዊ፣ ይኑር ቃልኪዳን ጠብቆ።*

## ለኢትዮጵያዊያን የአድዋ ድል በዓል መታሰቢያ                    የጐንቻው

Yegonchaw@yahoo.co.uk

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!